የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት
ETHIOPIAN PHARMACEUTICALS SUPPLY SERVICE

መመሪያ ቁጥር 1149/2019

የመድኃኒት ፍላጎትና ክምችት፣ መጋዘን አያያዝ እና ስርጭት አስተዳደር መመሪያ

DIRECTIVE No. 1149/2026

PHARMACEUTICAL DEMAND, INVENTORY, WAREHOUSE AND DISTRIBUTION MANAGEMENT DIRECTIVE

መስከረም፣ 2019 ዓ.ም

September፣ 2026

መመሪያ ቁጥር 1149/2019
የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት የመድኃኒት ፍላጎትና ክምችት፣ መጋዘን አያያዝ እና ስርጭት አስተዳደር መመሪያ

DIRECTIVE No. 1149/2026
PHARMACEUTICAL DEMAND, INVENTORY, WAREHOUSE AND DISTRIBUTION MANAGEMENT DIRECTIVE

ወቅቱን ያገናዘበ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበት የመድኃኒት ፍላጎትና ክምችት፣ መጋዘን አያያዝ እና ስርጭት አስተዳደር እና የአሰራር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas it has become necessary to put in place a timely, efficient, transparent, and accountable pharmaceutical demand, inventory, warehouse, and distribution management and operating system;

የአገልግሎቱ ማቋቋሚያ አዋጅ መቀየሩን ተከትሎ አዲስ አደረጃጀትና የአሰራር ስርአት የተዘረጋ እንዲሁም የመረጃ ስርአት በመቀየሩ ቀደም ሲል በስራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን በአዲስ መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፤

Whereas, following the change of the service's establishment proclamation, a new organizational structure and operating system have been put in place, and the information system has also been changed, making it necessary to replace the directives previously in effect with new directive;

የኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ አገልግሎት በኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ አገልግሎትና ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1354/2017 አንቀጽ 28(2) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

The Ethiopian Pharmaceuticals Supply Service has issued this directive pursuant to Article 28(2) of the Ethiopian Pharmaceuticals Supply Service and Fund Establishment Proclamation No. 1354/2017.

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

CHAPTER ONE
GENERAL PROVISIONS

1. አጭር ርዕስ

1. Short Title

ይህ መመሪያ "የመድኃኒት ፍላጎትና ክምችት፣ መጋዘን አያያዝ እና ስርጭት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 1149/2019" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

This Directive may be cited as **"The Ethiopian Pharmaceuticals Supply Service Pharmaceutical Demand and Inventory, Warehouse and Distribution Management Directive No. 1149/2026."**

2. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የኃረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "አገልግሎቱ" ማለት የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ነው።

2/ "ቅርንጫፍ" ማለት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ በአገልግሎቱ ስር የሚተዳደሩና ለጤና ተቋማት የመድሃኒት አቅርቦት አገልግሎት የሚሰጡ ቅርንጫፎች ናቸው።

3/ "ተቆጣጠሪ አካል" ማለት መድሃኒቶችን እንዲመዘግብ፣ ደህንነታቸውንና ፈዋሽነታቸውን እንዲቆጣጠር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው።

4/ "የሽያጭ ደረሰኝ" ማለት አቅራቢ ስለሚልከው የግዥ ትእዛዝ ቁጥር፣ የሽያጭ ደረሰኝ ቁጥር፣ የአቅራቢዉ ስም፣ የተቀባይ ስም፣ የመድኃኒቱ ስም፣ መጠን፣ዋጋ፣ የሽረት ጊዜ፣ የምርት መለያ ቁጥር፣ እና ተያያዥ የሆነ ሌሎች መረጃዎችን የያዘ ሰነድ ነው።

6/ "የመድሃኒት ዝርዝር መግለጫ" ማለት በእያንዳንዱ ጥቅል እሽግ ውስጥ ያለውን የመድኃኒት ዝርዝር በባች፣ በቁጥር፣ በመጠን እና በመጠቀሚያ ጊዜ ለይቶ በዝርዝር መረጃ የሚሰጥ ሰነድ ነው።

7/ "የክትባት መድረስ ማረጋገጫ ሰነድ" ማለት የክትባት መድኃኒቶች ወደ ማዕከላዊ መጋዘን ሲደርሱ በመጋዘን ኃላፊው እና በሚመለከተዉ የክምችት አስተዳደር ባለሙያ የሚሞላ ሲሆን አጠቃላይ የጉዞ ታሪክን ይይዛል።

8/"የመድኃኒት ገቢ ማረጋገጫ ሰነድ " ማለት የራሱ መለያ ቁጥር ያለው ሆኖ የመድኃኒቱን ዋጋ፣ የግዥ ትዕዛዝ ቁጥር፣ የሽያጭ ደረሰኝ

2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Directive:

1/ "Service" means the Ethiopian Pharmaceuticals Supply Service.

2/ "Branch" means the entities found in various parts of the country, administered under the Service, which provide pharmaceutical supply services to health facilities.

3/ "Regulatory Body" means the entity legally authorized to register and regulate the safety and efficacy of pharmaceuticals

4/"Commercial Invoice" means a document sent by the supplier containing the purchase order number, sales invoice number, supplier's name, recipient's name, name of the pharmaceutical, quantity, price, expiry date, batch/lot number, and other related information.

6/"Packing List" means a document providing detailed information distinguishing, by batch, quantity, amount and expiry date, the pharmaceutical contained in each package.

7/ "Vaccine Arrival Confirmation Document" means a document completed by the warehouse manager and the relevant expert when vaccines arrive at the central warehouse, which records the overall shipment history.

8/"Goods Receipt Voucher" means a document bearing its own reference number, confirming that the pharmaceutical has been entered into the

ቁጥር/ የክምችት ማስተላለፊያ መለያ ቁጥር፣ የጭነት መለያ ቁጥር፣ የመድኃኒቱን ስም፣ መለኪያ፣ ብዛት፣ መለያ ቁጥር፣ የሽረት ጊዜ፣ የአምራች ስም፣ መድኃኒቱ ሰነድ የያዘበት ቀን እና ሌሎችንም መረጃዎች የያዘ መድኃኒቱ ወደ አገልግሎቱ የመረጃ ቋት መግባቱን ማረጋገጫ ሰነድ ነው።

Service's database, and containing price, purchase order number, commercial invoice number/stock-transfer voucher number, airway/bill of loading reference number,, the Pharmaceutical name, unit of measure, quantity, batch number, expiry date, manufacturer name, date of received, and other information.

9/"የመድኃኒት መቀበያ ሰነድ" ማለት መድሃኒት በአቅራቢ ተጓጉዞ መጋዘን ሲደርስ የመጋዘን ኃላፊ በጥቅል ስለመቀበሉ የሚሰጠው ሰነድ ነው።

9/"Pharmaceutical Receiving Document" means a document issued by the warehouse manager confirming receipt of pharmaceuticals in bulk upon its arrival at the warehouse.

10/"የመድሃኒት መሰብሰቢያ ሰነድ" ማለት የክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ እንዲዘጋጅ ማዘዣ እና ክምችቶቹን ከማከማቻ ቦታ ወደ ማስረከቢያ ቦታ እንዲሰበሰቡ የሚደረግበት ሰነድ ነው።

10/"Picklist" means a document that serves as an instruction for preparing the stock to be dispatched and for collecting from the storage area to the dispatch area.

11/"የክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ" ማለት መድሃኒት ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ፣ ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፍ፣ ከቅርንጫፍ ወደ ዋናው መስሪያ ቤት እንዲሁም ከመጋዘን ወደ መጋዘን ለማስተላለፊያ የሚያገለግል ሰነድ ሆኖ የተቀባይ ተቋም ስም፣ መድኃኒቱ ወጪ የተደረገበት መጋዘን፣ መድኃኒቱ ወጪ የተደረገበት ቀን፣ የመድኃኒቱን ስም፣ መለኪያ፣ ብዛት፣ የመድኃኒቱን ዋጋ፣ የገንዘብ ምንጭ፣ የአምራች ስም፣ ባች ቁጥር፣ የሽረት ጊዜ እና ሌሎችንም መረጃዎች የያዘ ሰነድ ነው።

11/"Stock-Transfer Voucher/STV " means a document used to transfer Pharmaceutical from the Head Office to a Branch, from a Branch to another Branch, from a Branch to the Head Office, and from one warehouse to another, which containing the name of the receiving facility, the warehouse from which the pharmaceutical was issued, the issue date, name, unit of measure, quantity, price, source of funds, manufacturer, batch number, expiry date, and other information.

12/"መጋዘን" ማለት ገቢ የሚደረጉ መድኃኒቶች መረከቢያ፣ ማከማቻ እና ለተረካቢ ማስተላለፊያ ቦታ ያሉት ሲሆን የደረቅና የቀዝቃዛ መጋዘን አይነቶችን ያጠቃልላል።

12/"Warehouse" means a place having areas for pharmaceutical receiving, storing and transferring to a recipient, and includes both dry and cold storage warehouses.

13/"የቀዝቃዛ ሰንሰለት መጋዘን" ማለት ልዩ የቅዝቃዜ ባህርይ ያላቸው መድሃኒቶች ጥራታቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ የሚከማቹበት መጋዘን ነው።

13/"Cold Chain Warehouse" means a warehouse in which pharmaceuticals with special refrigeration requirements are stored in a manner that preserves their quality and safety.

14/"የመድሃኒቶች ክሮስ ዶክ" ማለት መድሃኒቶች በቀጥታ ከአቅራቢ ወደ ቅርንጫፍ ወይም ወደ ጤና ተቋም አስፈላጊውን ሰነድ በማሟላት የሚከናወንበት የስርጭት አሰራር ነው።

14/ "Cross-Docking of Pharmaceuticals" means a distribution arrangement whereby pharmaceuticals are delivered directly from a supplier to a Branch or health facility upon completion of the necessary documentation.

15/ "መጋዘን አስተዳደር" ማለት የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘን አስተዳደርን ለመጥቀስ ሲሆን በመጋዘን ውስጥ የሚከናወኑ የመድሃኒቶች ገቢ እና ወጪ ሲደረጉ የሚከናንወኑ ክንዋኔዎችን እንዲሁም የክምችት ቁጥጥር ስራዎችን ያካትታል።

15/ "Warehouse Management" refers to the management of the pharmaceutical storage warehouse, and includes the operations carried out when pharmaceuticals are received into and issued out of the warehouse, as well as stock-control activities.

16/ "የክምችት ቁጥጥር" ማለት በመጋዘን ውስጥ የክምችትን ደህንነት የማስጠብቅ እንዲሁም የክምች ትክክለኛነትን የማረጋገጥ ስራዎችን ያካትታል።

16/ "Inventory Control" includes activities of safeguarding the security of stock within the warehouse and of confirming inventory accuracy.

17/ "ክምችት" ማለት በአገልግሎቱ መጋዘን ዉስጥ የሚገኙ የተለያዩ መድኃኒቶች መጠን እና አይነት ማለት ነው።

17/ "Inventory" means the quantity and type of the various pharmaceuticals found in the Service's warehouse.

18/ "የመድሃኒት ገቢ ማድረጊያ ማዘዣ ቁጥር" ማለት መድሃኒት ከአቅራቢ ወደ ዋና መስሪያ ቤት መጋዘን ወይም ቅርንጫፍ መጋዘን ገቢ በሚደረግበት ወቅት ለማስተላለፊያነት የሚያገለግል በአገልግሎቱ የሚፈጠር የመረከቢያ ቁጥር ነው።

18/ "Inbound Delivery Number" means a receiving number generated by the Service, used for transfer purposes, at the time Pharmaceuticals is received into the Head Office or a Branch warehouse from a supplier.

19/ "ብዝሃ አቅራቢ ስርአት" ማለት በአቅርቦት አገልግሎት ስርአት ዉስጥ ብዛት ያላቸው የመድሃኒት አቅራቢዎች መድሃኒት ለጤና ተቋማት እንዲያቀርቡ የሚፈቅድ ስርአት ማለት ነው።

19/ "Multi Vendor System" means a system that allows a number of pharmaceutical suppliers, within the supply service system, to supply pharmaceuticals to health facilities.

20/ "የተገላባጭ ፈንድ መድኃኒት/መደበኛ" ማለት በአገልግሎቱ በተገላባጭ ፈንድ ተገዝቶ የሚቀርብ መድኃኒት ማለት ነው።

20/ "Revolving Drug Fund Medicine/Regular" means Pharmaceutical procured and supplied by the Service through the Revolving Fund.

21/ "የጤና ፕሮግራም መድሃኒት" ማለት በጤና ሚኒስቴር ወይም በሌሎች አጋር ድርጅቶች በኩል በሚገኝ ገንዘብ ተገዝቶ ወይም በአይነት ተለግሶ በአገልግሎቱ አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ተከማችቶ ክፍያ ሳይጠየቅበት ስርጭት የሚከናወንለት መድሃኒት ነው።

21/ "Health Program Medicine" means Pharmaceutical procured with funds obtained through the Ministry of Health or other partner organizations, or donated in kind, stored within the Service's supply chain, and distributed without charge.

22/ "አማካይ ወርሃዊ ፍጆታ" ማለት አንድ መድኃኒት በአማካይ በወር ውስጥ ምን ያህል እንደተሰራጨ ወይም ጥቅም ላይ እንደዋለ የሚያመለክት መጠን ነው።

22/ "Average Monthly Consumption" means the quantity indicating how much of a given Pharmaceutical is, on average, distributed or utilized in a month.

23/ "የመጠባበቂያ ክምችት መጠን" ባልተጠበቀ የፍጆታ መጨመር፣ የአቅርቦት ጊዜ ከተጠበቀው በላይ መዘግየት እና በተለያዩ ሁኔታዎች ምክንያት በድንገት ለሚከሰት የክምችት መሳሳት ሊያገለግል የሚችል የክምችት መጠን ነው።

23/ "Safety Stock Level" means the quantity of stock that can be used to cover stock shortfalls arising unexpectedly from an unforeseen increase in consumption, a delay in the lead time beyond what is expected, or other various circumstances.

24/ "ዝቅተኛ የክምችት መጠን" ማለት በአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ ወይም በጤና ተቋም ቢያንስ በክምችት ሊኖር የሚገባው መጠን ነው።

24/ "Minimum Stock Level" means the quantity that must, at a minimum, be held in stock at the Service's Head Office and Branch, or at a health facility.

25/ "ከፍተኛ የክምችት መጠን" ማለት በአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ ወይም በጤና ተቋም በክምችት ሊኖር የሚገባው ከፍተኛ መጠን ነው።

25/ "Maximum Stock Level" means the quantity that should, at most, be held in stock at the Service's Head Office, Branch, or at a health facility.

26/ "የፍላጎት አስተዳደር" ማለት የጤና ተቋማት የመደበኛ እና የጤና ፕሮግራም የመድኃኒት ፍላጎትን ከአቅርቦት ጋር በማጣጣም ማስተዳደር ነው።

26/ "Demand Management" means managing the matching of health facilities' regular and health-program pharmaceutical demand with supply.

27/ "የአቅርቦት እቅድ" ማለት በክምችት እና በግዥ ሂደት ላይ ያለውን የመድሃኒት መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት የጤና ተቋማትን ወቅታዊ ፍላጎት ለሚሟላት የሚያስችል እቅድ ነው።

27/ "Supply Plan" means a plan enabling the current demand of health facilities to be met, having regard to the quantity of Pharmaceutical in stock and in the procurement process.

28/ "የክምችት ክትትል" ማለት የአቅርቦት ክፍተት እንዳይፈጠር በዋናው መስሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ መጋዘኖች ውስጥ ያለውን የመድኃኒት ክምችት እና በግዥ ሂደት ያለውን መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የክትትል ስርዓት ነው።

28/ "Inventory Monitoring" means a monitoring system enabling necessary measures to be taken, having regard to the pharmaceutical stock in the central and Branch warehouses and the quantity in the procurement process, so as to prevent a supply gap from arising.

29/ "ግምታዊ መሸጫ ዋጋ" ማለት አገልግሎቱ ለጤና ተቋማት በሚቀጥለው በጀት አመት የመድሃኒት ግዥ እቅድ ስራ እንዲረዳቸው የሚልክላቸው ግምታዊ የመድሃኒት መሸጫ ዋጋ ማለት ነው።

29/ "Estimated Selling Price" means the estimated pharmaceutical selling price sent by the Service to health facilities to assist them in their pharmaceutical procurement planning for the following budget year.

30/ "ግምታዊ የመግዣ ዋጋ" ማለት ጤና ተቋማት በሚቀጥለው በጀት ዓመት የመድሃኒት ግዥ እቅድ ሲሰሩ የሚጠቀሙበት ግምታዊ የመድሃኒት መግዣ ዋጋ ነው።

30/ "Estimated Purchase Price" means the estimated pharmaceutical purchase price used by health facilities when preparing their pharmaceutical procurement plan for the following budget year.

31/ "የመድሃኒት ስርጭት መርሀ ግብር" ማለት መድኃኒት ከዋናው መስሪያ ቤት ለቅርንጫፍ ወይም ከቅርንጫፍ ለጤና ተቋም የሚሰራጭበት የጊዜ ሰሌዳ ነው።

31/ "Pharmaceutical Distribution Schedule" means the timetable by which Pharmaceutical is distributed from the Head Office to a Branch, or from a Branch to a health facility.

32/ "የመድሃኒት ስርጭት አስተዳደር" ማለት መድሃኒትን ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ ወይም ከቅርንጫፍ ወደ ጤና ተቋም ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በወቅቱ እንዲደርሱ የሚደረግበት የአስተዳደር ስርዓት ነው።

32/ "Pharmaceutical Distribution Management" means the management system by which Pharmaceuticals are made to arrive safely and on time from the Head Office to a Branch, or from a Branch to health facilities.

33/ "የኮንትራት አስተዳደር" ማለት በአገልግሎቱ ዋናው መስሪያ ቤት ግዥ ተፈጽሞላቸው ወደ መጋዘን ገቢ እስኪደረጉና ለአገልግሎት ዝግጁ

33/ "Contract Management" means the system for executing the process from the completion of procurement by the Service's Head Office until

እስኪሆኑ ድረስ ያለውን ሂደት የማስፈፀም ስርዓት ነው።

34/ "ሞዴል-19" ማለት ተረካቢው ከአገልግሎቱ ዋናው መስሪያ ቤት ወይም ከቅርንጫፍ ለጤና ተቋም መድሃኒት ስለማስረከቡ የሚሰጠው የገቢ ማረጋገጫ ሰነድ ሲሆን የተቋሙን ስም የሰነድ ቁጥር፣ የአስረካቢውን ተቋም ስም፣ ቀን፣ እነዲሁም የመድሃኒት ስም ዝርዝር፣ መለኪያ፣ ብዛት፣ ዋጋ፣ የምርት መለያ ቁጥር፣ የአስረካቢ፣ የተረካቢ ስምና ፊርማ ያረፈበትና ሌሎችንም ይይዛል።

35/ "ድንገተኛ አደጋ" ማለት በተለያየ ምክንያት በመድሃኒት ስርጭት ስራ ወቅት ሊከሰት የሚችል ጉዳት ማለት ነው።

36/ "ልዩ ባህሪ ያላቸው መድሃኒቶች" ማለት መድሃኒቶች በጭነትና በማጓጓዝ ሂደት ላይ እንዳይሰበሩ ወይም እንዳይበላሹ ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የቅዝቃዜ ሰንሰለት የሚፈልጉ ክትባቶችን፣ የተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸውን ኬሚካልና ሪኤጀንት በቀላሉ የሚሰበሩና የሚፈሱ መድሃኒቶችንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

37/ "መንግስታዊ ጤና ተቋም" ማለት በመንግስት የተቋቋሙ ለህብረተሰቡ የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ማለት ነው።

38/ "የግል ጤና ተቋም" ማለት በግሉ ዘርፍ መዋዕለ ንዋይ የተቋቋመ ለህብረተሰቡ የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ማለት ነው።

39/ "መንግስታዊ ያልሆኑ ጤና ተቋም" ማለት በተለያየ የአጋር ድርጅት፣ በልማት ድርጅት፣ በበጎ አድራጎት ድርጅት፣ በማህበራት ወይም በመሳሰሉት የግንዘብ ድጋፍ የተቋቋመ ለህብረተሰቡ የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ማለት ነው።

goods are received into the warehouse and made ready for service.

34/ "Model-19" means the goods-receipt confirmation document issued confirming that a recipient health facility has received Pharmaceutical from the Service's Head Office or a Branch containing the facility's name, document number, the delivering facility's name, date, list of Pharmaceutical names, unit of measure, quantity, price, product reference number, and the names and signatures of the deliverer and recipient, among other things.

35/ "Emergency Accident" means damage that may occur during Pharmaceuticals distribution operations due to various causes.

36/ "Pharmaceuticals with Special Characteristics" means Pharmaceuticals requiring special care to prevent breakage or damage during loading and transport, and includes vaccines requiring a cold chain, flammable chemicals and reagents, easily breakable or spillable Pharmaceuticals, and the like.

37/ "Government Health facility" means a facility established by the government to provide health services to the public.

38/ "Private Health facility" means a facility established with private-sector capital to provide health services to the public.

39/ "Non-Governmental Health facility" means a facility established with financial support from a partner organization, development organization, charitable organization, association, or the like, to provide health services to the public.

40/ "የጉዞ መስመር" ማለት ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ ወይም ከቅርንጫፍ ወደ ጤና ተቋም ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መድኃኒት ለማድረስ የምንጠቀምበት መንገድ ነው።

40/ "Distribution Route" means the route used to deliver Pharmaceutical, in a time- and cost-efficient manner, from the Head Office to a Branch, or from a Branch to a health facility.

41/ "አዋጅ" ማለት በኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ አገልግሎትና ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1354/2017 ነው።

41/ "Proclamation" means the Ethiopian Pharmaceuticals Supply Service and Fund Establishment Proclamation No. 1354/2017.

42/ በአዋጁ ላይ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች ለዚህም መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናል።

42/ Terms and phrases defined in the Proclamation shall apply equally to this Directive.

43/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸ አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል።

43/ Any expression stated in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአገልግሎቱ በዋናዉ መስሪያ ቤት፣ በቅርንጫፎች እና በጤና ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3. <u>Scope of Application</u>

This Directive shall apply to the Service's Head Office, its Branches, and health facilities.

<u>ክፍል ሁለት</u>
<u>የመድኃኒት ፍላጎት እና ክምችት አስተዳደር</u>
<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
<u>የአቅርቦት እቅድ እና ክምችት አስተዳደር</u>

<u>CHAPTER TWO</u>
<u>PHARMACEUTICAL DEMAND AND INVENTORY MANAGEMENT</u>
<u>Section One</u>
<u>Supply Planning and Inventory Management</u>

4. <u>የመደበኛ መድኃኒት የአቅርቦት ዕቅድ አዘገጃጀትና አወሳሰን</u>

የጤና ተቋም ዓመታዊ የመደበኛ በጀት የመድኃኒት ፍላጎት በአገልግሎቱ ቅርንጫፍ በኩል እንደሚከተለው የሚቀርብ ይሆናል፡-

4. <u>Preparation and Approval of the Regular Pharmaceutical Supply Plan</u>

The annual regular-budget pharmaceutical demand of a health facility shall be submitted through the Service's Branch as follows:

1/ በአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊ የጸደቀ የመድሃኒት መዘርዝር ከወቅታዊ ግምታዊ መሸጫ ዋጋ ጋር በማዘጋጀት በየዓመቱ ለጤና ተቋም ያሳውቃል።

1/ The Service shall annually prepare and disseminate to health facilities a list of Pharmaceuticals, including their current estimated selling prices, upon approval by the Head of the Service

2/ ጤና ተቋም ከአገልግሎቱ በተላከው የመድሃኒት መዘርዝር መሰረት በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ ፍላጎቱን በአገልግሎቱ ቅርንጫፍ በኩል ያሳውቃል።

2/ The health facility shall notify its budget-supported annual demand, based on the list of Pharmaceuticals sent by the Service, through the Service's Branch.

3/ ጤና ተቋም ከአገልግሎቱ ከተላከው የመድሃኒት መዘርዝር ውጪ ተጨማሪ ፍላጎት ካለው በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ ፍላጎቱን ለአገልግሎቱ ቅርንጫፍ ማሳወቅ ይችላል።

3/ If the health facility has additional demand beyond the list of Pharmaceuticals sent by the Service, it may notify its budget-supported annual demand to the Service's Branch.

4/ ከጤና ተቋም የሚቀርብ ማንኛውም ዓመታዊ የመድሃኒት ፍላጎት በጤና ተቋሙ የበላይ ሃላፊ የጸደቀ መሆን ይኖርበታል።

4/ Any annual pharmaceutical demand submitted by a health facility must be approved by the head of that health facility.

5/ በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ የጤና ተቋም የመደበኛ በጀት መድሃኒት ፍላጎት በአገልግሎቱ ቅርንጫፍ ተሰብስቦ፣ተቀናጅቶ እና ተጠናቅሮ ለአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት ይላካል።

5/ The budget-supported annual regular pharmaceutical demand of health facility shall be collected, consolidated and compiled by the Service's Branch and forwarded to the Service's Head Office.

6/ በቅርንጫፍ በኩል ተጠናቅሮ የተላከው የጤና ተቋም ዓመታዊ የመድሃኒት ፍላጎት በአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት በመተንተን እና በማጠናቀር አመታዊ የመድሃኒት ፍላጎት ያዘጋጃል::

6/ The Service shall prepare its annual pharmaceutical demand by analyzing and consolidating the annual pharmaceutical requirements submitted by health facilities through the branch offices.

7/ ከቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ስርዓት ውጪ የሆነ መድሃኒት በብዝሃ አቅራቢ ስርዓት እንዲቀርብ አሰራር ይዘረጋል።

7/ For Pharmaceutical not covered under the committed demand and supply system, an arrangement shall be established for it to be supplied through the multi-vendor system.

8/ የቅድሚያ ውል ለተገባበት፤ በብዝሃ አቅራቢ ስርዓት እና በሌላ አማራጭ የሚቀርብ

8/ The list of Pharmaceuticals to be supplied under the committed demand and supply system, , the multi-vendor system , or by other alternative shall

የመድሃኒት ዝርዝር ጤና ሚኒስቴር፣ ክልል ጤና ቢሮ፣ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ እና ጤና ተቋም እንዲያውቁት ይደረጋል።

be communicated to the Ministry of Health, Regional health bureaus, city administration health bureaus, and health facility.

9/ አገልግሎቱ የቅድሚያ ውል ለተገባበት የአቅርቦት ስርዓት ለሚቀርብ መድሃኒት ከጤና ተቋም ጋር የአቅርቦት ውል ይገባል።

9/ The Service shall enter into a contract agreement with health facilitys for the provision of pharmaceuticals under the committed demand and supply system

10/ ቅድሚያ ውል ለተገባበት የአቅርቦት ስርዓት ለሚቀርብ መድሃኒት የአቅርቦት እቅድ በመስራት ለግዥ አስተዳደር ይቀርባል እንዲሁም በብዝሃ አቅራቢ ስርዓት ተለይቶ የሚቀርብ መድሃኒት ለግዥ አስተዳደር ይቀርባል።

10/ The Service shall prepare a supply plan for pharmaceuticals to be procured under the committed demand and supply system and submit the procurement request to the Procurement Management Directorate. The Service shall also submit to the Procurement Management Directorate the list of pharmaceuticals to be procured through the multi-vendor procurement system.

11/ በየሩብ ዓመቱ የፍላጎት እና አቅርቦት መለዋወጥን ታሳቢ ያደረገ የአቅርቦት እቅድ ክለሳ በመስራት ለበላይ ሃላፊ ምክረ ሃሳብ በማቅረብ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል።

11/ The Service shall conduct the quarterly supply plan revision, by taking into consideration changes in pharmaceutical demand and supply and submit its recommendations to the appropriate authority. The revised supply plan shall be implemented in accordance with the directions issued by the appropriate authority.

5. <u>የጤና ፕሮግራም መድኃኒት የአቅርቦት ዕቅድ አዘገጃጀትና አወሳሰን</u>

5. <u>Preparation and Approval of the Health Program Pharmaceutical Supply Plan</u>

አገልግሎቱ፡-

The Service:

1/ በበጀት የተደገፈ የጤና ፕሮግራም ዓመታዊ የመድሃኒት ፍላጎት ከጤና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢኒስቲትዩት እና ከሌላ ተገልጋይ ተቋም ጋር በጋራ በመሆን ይሰራል።

1/ Shall jointly work out the budget-supported annual health-program pharmaceutical demand together with the Ministry of Health, the Ethiopian Public Health Institute, and other client facilities.

2/ ከጤና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢኒስቲትዩት እና ከሌላ ተቋም የግዥ ጥያቄ

2/ Shall receive and consolidate procurement requests from the Ministry of Health, the

በመቀበል እና በማጠናቀር የአቅርቦት እቅድ በመስራት ለግዥ አስተዳደር ያቀርባል።

Ethiopian Public Health Institute, and other facilities, prepare a supply plan, and submit the procurement request to the Procurement Management.

3/ በየሩብ ዓመቱ የፍላጎት እና አቅርቦት መለዋወጥን ታሳቢ ያደረገ የአቅርቦት እቅድ ክለሳ በመስራት እና ለጤና ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢኒስቲትዩት እና ሌላ ተገልጋይ ተቋም የምክረ ሃሳብ በማቅረብ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል።

3/ Shall carry out a quarterly supply plan revision, taking into account fluctuations in demand and supply, submit recommendations to the Ministry of Health, the Ethiopian Public Health Institute and other facilities, and implement in accordance with the resulting decision.

6. <u>አስቸኳይ ምላሽ ለሚሹ የሀገር አቀፍ የጤና ችግሮች የመድኃኒት አቅርቦት ዕቅድ ዝግጅት</u>

6. <u>Preparation of the Pharmaceutical Supply Plan for National Health Emergencies Requiring Urgent Response</u>

የአገልግሎቱ ፍላጎት እና ክምችት አስተዳደር አስቸኳይ ምላሽ ለሚሹ የሀገር አቀፍ የጤና ችግሮች የመድኃኒት አቅርቦት ዕቅድ ዝግጅት ሥራን የሚያከናውን ሲሆን አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

The Service's Demand and Inventory Management shall carry out the preparation of the pharmaceutical supply plan for national health emergencies requiring urgent response, and its execution shall be as follows:

1/ በሀገር አቀፍ ደረጃ በጤናው ዘርፍ በተቋቋመው የአደጋ ዝግጁነትና መላሽ ግብረ ሃይል ጋር በጋራ በመሆን ለችግሩ ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልግ የመድሃኒት ዝርዝር ይለያል።

1/ The Service shall, in collaboration with the established national health Emergency Preparedness and Response Task Force, identify the list of pharmaceuticals required to respond to public health emergencies.

2/ በሀገር አቀፍ ደረጃ በጤናው ዘርፍ በተቋቋመው የአደጋ ዝግጁነትና መላሽ ግብረ ሃይል ጋር በጋራ በመሆን ለችግሩ ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልግ የመድሃኒት ዝርዝር መሰረት የመድሃኒት ፍላጎት ትንበያ እንዲሰራ ያደርጋል።

2/ With the national Emergency Preparedness and Response Task Force, the Service shall conduct a pharmaceutical demand forecast based on the identified list of medicines required to respond to emergencies.

3/ በአገልግሎቱ መጋዘኖች በክምችት እና በግዥ ሂደት ላይ ያለውን የመድሃኒት መጠንና

3/ The Service shall conduct a supply plan by considering the quantity and type of pharmaceuticals available in its warehouses and

አይነት በማካተት የግዥ እቅድ በመስራት ለግዥ አስተዳደር ያቀርባል።

4/ በመደበኛ በጀት ክምችት ያለ መድሃኒት ከሚመለከተው አካል በሚመጣ ጥያቄ መሰረት በቂ በጀት መያዙን በማረጋገጥ በአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊ ሲፈቀድ ሽያጭ ያከናውናል።

5/ በጤና ፕሮግራም ክምችት ያለ መድሃኒት ከጤና ሚኒስቴር በሚመጣ ጥያቄ መሰረት በአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊ ሲፈቀድ ስርጭት ያከናውናል።

6/ በክምችት እና በግዥ ሂደት ላይ በበቂ መጠን የማይገኘውን መድሃኒት የበጀት ምንጩን በመግለጽ ግዥ እንዲፈጸም ለግዥ አስተዳደር ጥያቄ በማቅረብ ክትትል ያደርጋል።

7. <u>የመድኃኒት የክምችት እና አቅርቦት ክትትል ስርዓት</u>

የአገልግሎቱ የመድኃኒት ፍላጎት እና ክምችት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የክምችት እና አቅርቦት ክትትል ሥራን የሚያከናውን ሲሆን አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1/ በጤና ሚኒስቴር በተሻሻለው ተገቢ የመድሃኒት ክምችት መመሪያ መሰረት የመድሃኒት ክምችት በአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ እንዲሁም በጤና ተቋም በከፍተኛ እና ዝቅተኛ ክምችት መጠን እንዲገኝ ለማድረግ የግዥ የጊዜ ሰሌዳ፣ አማካይ ወርሃዊ ፍጆታ፣ ለማቅረብ የሚወስደው ጊዜ፣ የመጠባበቂያ ክምችት መጠን፣ የመጋዘኖች

pipeline inventories and submit the procurement request to the Procurement Management Directorate.

4/ The Service shall sale pharmaceuticals managed under the regular medicine upon receiving a request from the concerned entity, after verifying the availability of adequate budget allocation and obtaining approval from the Head of the Service

5/ Based on a request from the Ministry of Health regarding Pharmaceutical held in health-program stock, it shall carry out distribution upon approval of the head of the Service.

6/ The Service shall identify pharmaceuticals that are not sufficiently available in stock or pipeline, submit a procurement request to the Procurement Management Directorate indicating the budget source, and follow up on the procurement process.

7. <u>Pharmaceutical Stock and Supply Monitoring System</u>

The Service's Pharmaceutical Demand and Inventory Management Directorate shall carry out inventory and supply monitoring, and its execution shall be as follows:

1/ In accordance with the revised Pharmaceutical Inventory Holding Guideline issued by the Ministry of Health, the Service shall ensure that pharmaceutical stock levels are maintained within the established minimum and maximum stock limits at the Service's head office, branches and health facilities. In determining the appropriate stock levels, the Service shall consider the delivery schedule, average monthly consumption, delivery lead time, safety stock

የማከማቸት አቅም እና የፍጆታ መረጃ ታሳቢ ያደርጋል።

requirements, warehouse storage capacity, and consumption data.

2/ በጤና ሚኒስቴር የመድሃኒት ክምችት መምሪያ ላይ ስለ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ክምችት መጠን የተቀመጠው ቢኖርም የመጋዘን ቦታ ጥበት በሚያጋጥም ወቅት ወይም በመድሃኒቱ ልዩ ባህሪ ምክንያት በጊዜያዊነት እንዲቀመጥ ወደ አገልግሎቱ ቅርንጫፍ የማስተላለፍ እና እንዳስፈላጊነቱ ወደ ጤና ተቋም እንዲሰራጭ ያደርጋል።

2/ Notwithstanding the minimum and maximum pharmaceutical stock levels established under the revised Pharmaceutical Inventory Holding Guideline of the Ministry of Health, where warehouse space constraints arise or where the pharmaceutical nature so requires, the Service may, on a temporary basis, transfer such pharmaceuticals to its branch and, where appropriate, distribute them to health facilities as operationally necessary.

3/ የመድሃኒት ክምችት በዋና መስሪያ ቤት በቅርንጫፍ በከፍተኛ እና ዝቅተኛ ክምችት መጠን መካከል መሆኑን ለማረጋገጥ የክምችት ትንተና በመስራት ለውሳኔ ያቀርባል።

3/ It shall carry out stock analysis to confirm that pharmaceutical stock at the Head Office and Branch is maintained between the maximum and minimum stock levels, and submit it for a decision.

4/ በአገልግሎቱ መጋዘኖች ተገቢው የመደበኛ መድሃኒት ክምችት መኖሩን ለማረጋገጥ የተለያዩ የክምችት ትንተና ዘዴዎችን በመጠቀም የክምችት ትንተና በመስራት ለበላይ ሃላፊ ምክረ ሃሳብ በማቅረብ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል።

4/ Using various stock-analysis methods, it shall carry out stock analysis to confirm that appropriate regular pharmaceutical stock exists in the Service's warehouses, submit recommendations to the head, and implement in accordance with the decision given.

5/ በአገልግሎቱ መጋዘኖች ተገቢው የጤና ፕሮግራም መድሃኒት ክምችት መኖሩን ለማረጋገጥ የተለያዩ የክምችት ትንተና ዘዴዎችን በመጠቀም የክምችት ትንተና በመስራት የጤና ሚኒስቴር ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ምክረ ሃሳብ በማቅረብ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል።

5/ Using various stock-analysis methods, it shall carry out stock analysis to confirm that appropriate health-program pharmaceutical stock exists in the Service's warehouses, submit recommendations to the Ministry of Health, and implement in accordance with the decision given.

6/ የአቅርቦት ክፍተት እንዳይፈጠር በአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ መጋዘኖች ውስጥ ያለውን የመድኃኒት ክምችት እና

6/ The Service shall conduct continuous stock status monitoring at its head office and branch warehouses by assessing available pharmaceutical stock and quantities in the

በግዥ ሂደት ያለውን መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት የክምችት ክትትል ያደርጋል።

7/ በተሰራው የክምችት ትንተና መሰረት በጤና ተቋም ላይ የመድሃኒት ግኝት እና አጠቃቀም ዙሪያ ያሉ ችግሮች መንስኤዎችን በመለየት ውጤቱን ለጤና ሚኒስቴርና ለባለድርሻ አካላት ያሳውቃል።

pipeline to ensure uninterrupted supply and prevent stock shortages.

7/ Based on the stock analysis carried out, it shall identify the causes of problems relating to the availability and use of Pharmaceutical at a health facility, and communicate the findings to the Ministry of Health and stakeholders.

ንዑስ ክፍል ሁለት
የመድሃኒት ጥያቄ እና አቅርቦት አስተዳደር ስርዓት

Section Two
Pharmaceutical Request and Supply Administration System

8. የቅርንጫፍ ጥያቄ እና አቅርቦት አስተዳደር ስርአት

አገልግሎቱ የመደበኛና የጤና ፕሮግራም መድሃኒቶችን በጤና ተቋም ጥያቄ መሰረት የስርጭት ሥራ የሚሠራ ሲሆን አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ይሆናል፦

1/ ከጤና ተቋም የሚቀርበውን የመድኃኒት ጥያቄ ይቀበላል እንዲሁም ይመዘግባል።

2/ የቀረበውን ጥያቄ በቅርንጫፍ ወይም በአገልግሎቱ ዋና መሥሪያ ቤት ካለው የክምችት መረጃ ጋር በማነጻጸር ያረጋግጣል።

3/ ተቀባይነት ያገኘውን የመድኃኒት ጥያቄ መሠረት በማድረግ የወጪ ማዘዣ ያዘጋጃል።

4/ የተዘጋጀውን የወጪ ማዘዣ መሠረት በማድረግ መድኃኒቱ ለጤና ተቋም እንዲደርስ ክትትል ያደርጋል።

8. Branch Request and Supply Administration System

The Service shall carry out distribution of regular and health-program Pharmaceuticals based on the request of a health facility, and its execution shall be as follows:

1/ It shall receive and register the pharmaceutical request submitted by the health facility.

2/ It shall verify the submitted request by comparing it with the stock information held at the Branch or the Service's Head Office.

3/ It shall prepare an issue voucher based on the approved pharmaceutical request.

4/ It shall follow up, on the basis of the prepared issue voucher, to ensure that the Pharmaceutical reaches the health facility.

9. <u>የመደበኛ መድሃኒት ጥያቄ እና አቅርቦት አስተዳደር ስርዓት</u>

1/ ጤና ተቋም አገልግሎቱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የመድኃኒት ጥያቄ ያቀርባል።

2/ ጤና ተቋም የቅድሚያ ውል በተገባለት የአቅርቦት ስርዓት መሰረት የሩብ ዓመት የግዥ እቅድ በማዘጋጀት ለአገልግሎቱ ቅርንጫፍ የግዥ ጥያቄ ያቀርባል።

3/ ጤና ተቋም ህጋዊ የውክልና ደብዳቤ፣ መድሃኒት ለመግዛት የተወከለው ባለሙያ ማንነትን የሚገልጽ የመስሪያ ቤቱ መታወቂያ፣ የመድኃኒት ዝርዝር፣ የታደሰ የመድሃኒት መግዣ ፍቃድ እንዲሁም ለዱቤ ግዥ አገልግሎት የዱቤ ግዥ ውል ያቀርባል።

4/ አገልግሎቱ ቅድሚያ ውል በተገባለት የአቅርቦት ስርዓት ውል መሰረት ከጤና ተቋም የመድሃኒት አቅርቦት ጥያቄ በመቀበል እና የክምችት ሁኔታን በማየት የመድኃኒት ወጭ ማዘጋጀት በማዘጋጀት ይከታተላል።

5/ አገልግሎቱ ቅድሚያ ውል የተገባለት መደበኛ መድኃኒት በክምችት አለመኖሩ በማረጋገጥ የመድሃኒቱ አለመኖር ማስረጃን ለጤና ተቋም ይሰጣል።

6/ አገልግሎቱ የዱቤ አገልግሎት የሚያገኝ ጤና ተቋም ግዥ ለመፈጸም በሚመጣበት ወቅት የግዥ ጥያቄው ከመስተናገዱ በፊት በገባው ውል መሰረት ከዚህ በፊት ለወሰደው መድሃኒት ክፍያ መፈጸሙን ያረጋግጣል።

9. <u>Regular Pharmaceutical Request and Supply Administration System</u>

1/ The health facility shall submit its pharmaceutical request in accordance with the schedule set by the Service.

2/ The health facility shall, in accordance with the framework-agreement supply system, prepare a quarterly procurement plan and submit a procurement request to the Service's Branch.

3/ The health facility shall submit a valid letter of delegation, an ID card of the professional delegated, list of pharmaceutical to be purchased, an updated pharmaceutical purchase license, and, for credit-purchase service, a credit-purchase agreement.

4/ In accordance with the framework agreement, the Service shall receive the pharmaceutical supply request from the health facility, review the stock situation, prepare a pharmaceutical issue voucher, and follow up.

5/ Where it is confirmed that regular pharmaceutical covered by the framework agreement is not in stock, the Service shall provide evidence of the Pharmaceutical's stockout to health facilities.

6/ Before processing the procurement request of a health facility having access to credit service, at the time it comes to make a purchase, the Service shall confirm that payment has been made, in accordance with the agreement entered into, for pharmaceutical previously received.

10. የጤና ፕሮግራም መድሃኒት ጥያቄ እና አቅርቦት አስተዳደር ስርዓት

1/ ጤና ተቋም በአገልግሎቱ ቅርንጫፍ በሚወጣለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መደበኛ የሪፖርት እና መጠየቂያ ቅጽ በተገቢው በመሙላት ያቀርባል።

2/ አገልግሎቱ ከጤና ተቋም የጤና ፕሮግራም መድሃኒት አቅርቦት ጥያቄ በመቀበል እና የክምችት ሁኔታን በማየት የመድኃኒት ወጪ ማዘጋጀ ያዘጋጃል።

3/ አገልግሎቱ ከጤና ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚመጡ የመድኃኒት ክፍፍል በመቀበልና የስርጭት ሰነድ በማዘጋጀት ወደ ጤና ተቋም ያደርሳል።

10. Health Program Pharmaceutical Request and Supply Administration System

1/ The health facility shall duly complete and submit the regular report and requisition form in accordance with the schedule set by the Service's Branch.

2/ The service shall receive the health facility's health-program pharmaceutical supply request, review the stock situation, prepare a pharmaceutical issue voucher, and follow up.

3/ The service shall receive pharmaceutical distribution coming from the Ministry of Health and other stakeholders, prepare a distribution document, and distributed to health facilities accordingly.

ንዑስ ክፍል ሶስት
የመረጃ አያያዝና ሪፖርት ስርአት

Section Three
Information Management and Reporting System

11. መሰረታዊ የመድኃኒት መረጃ አያያዝ እና አስተዳደር

በአገልግሎቱ የመረጃ ቋት እንደ አዲስ የሚመዘገቡ ወይም ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው መድሃኒቶችን በተመለከተ የአገልግሎቱ ፍላጎት እና ክምችት አስተዳደር የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

1/ ከግዥ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ ከመጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬትከጤና ሚኒስቴር ወይም ከጤና ተቋም የሚቀርቡ የመድኃኒት

11. Basic Pharmaceutical Information Management and Administration

With respect to pharmaceuticals to be newly registered or that require correction in the Service's database, the Service's Demand and Inventory Management shall carry out the following activities:

1/ It shall verify, through the Service's Head Office, the accuracy of pharmaceutical information-registration requests submitted by the

መረጃ ምዝገባ ጥያቄዎችን በአገልግሎቱ ዋና መሥሪያ ቤት በኩል ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጣል።

2/ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ የመድኃኒት መረጃዎች በማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ ይመዘግባል።

3/ በአገልግሎቱ ዋና መሥሪያ ቤት የተመዘገቡ መረጃዎች ለሥራ አመቺ እንዲሆኑ በሁሉም የአገልግሎቱ ቅርንጫፎች ወጥ በሆነ መልኩ እንዲሰሩ ያደርጋል።

4/ ከመረጃ ቋቱ እንዲወጡ በክፍሎች ጥያቄ የቀረበባቸው መድኃኒቶች መረጃ፣ የማጣራት ሥራ ተከናውኖና በበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ ብቻ እንዲሰረዝ ያደርጋል።

5/ በአገልግሎቱ የመረጃ ቋት ውስጥ ያልነበሩ መድሃኒቶች ወደ መረጃ ቋት እንዲገቡ ጥያቄ ሲቀርብና በበላይ ሃላፊ ሲፈቀድ አስፈላጊው ማጣራት በመስራት ወደ አገልግሎቱ የመረጃ ቋት ይመዘግባል።

Procurement Administration Directorate, the Warehouse Administration Directorate, the Ministry of Health, or a health facility.

2/ It shall register pharmaceutical information whose accuracy has been verified into the central database.

3/ It shall ensure that information registered at the Service's Head Office is applied uniformly across all Branches of the Service so as to facilitate operations.

4/ It shall cause information on Pharmaceuticals requested by departments to be removed from the database to be deleted only after a verification process has been carried out and approval given by the head.

5/ Where a request is submitted for pharmaceuticals not previously in the Service's database to be entered into the database, and it is approved by the higher officials, shall conduct the necessary verification and register them in the Service's database.

ክፍል ሦስት
የመጋዘን አስተዳደርና ክምችት ቁጥጥር
ንዑስ ክፍል አንድ
የመጋዘን አደረጃጀት፣ የክምችት ገቢ እና ወጪ ስርዓት

12. የመጋዘን የውስጥና የውጭ አደረጃጀት

1/ የአገልግሎቱ መጋዘን የጭነት ተሽከርካሪዎችን ከፍታ ታሳቢ ያደረገ ጭነት ለማራገፍና

CHAPTER THREE
Warehouse Management and Inventory Control
Section One
Warehouse Organization, Inventory Receipt and Issuance System

12. Internal and External Organization of the Warehouse

1/ The Service's warehouse shall have, depending on its layout, a loading area suited to the height of

ለመጫን የሚያመች በረንዳ እና በዝናብ ወቅት መድሃኒት እንዳይበላሽ እና የስራ እንቅስቃሴ እንዳይስተጓጎል የሚያግዝ ታፕ እንደመጋዘኑ የአቀማመጥ ሁኔታ ይኖረዋል።

vehicles for loading and unloading, and a canopy that helps to prevent pharmaceuticals from being damaged during the rainy season and prevents disruption of operations.

2/ የአገልግሎቱ መጋዘን የክምችት እንቅስቃሴና ቀልጣፋ አሰራር ለመተግበር በሚያስችል መልኩ በመጋዘን ውስጥ የመረከቢያ፣ የማከማቻ፣ የማስረከቢያ እና የመጋዘን መገልገያ መሳሪያዎች ማስቀመጫ ስፍራ ይኖራቸዋል።

2/ The Service's warehouse shall have designated receiving, storage, dispatching, and material handling equipment-storage areas within it, so as to enable stock movement and efficient operations.

3/ ለመጋዘን ኃላፊዎች እና ለመጋዘን ውስጥ ሰራተኞች የሚያግለግል ቢሮዎችና የሰነድ ማስቀመጫ ክፍሎች ይኖረዋል።

3/ It shall have offices and document-storage rooms to serve warehouse managers and other warehouse staff.

4/ ለአገልግሎቱ መጋዘን ስራ አስፈላጊ የሆነ ግብአት እንደ ፎርክሊፍት፣ ጋሪ፣ ፓሌት፣ የሀይል መጠባበቂያ ጀነሬተር፣ የሙቀትና እርጥበት መለኪያ መሳሪያ፣ እሳት ማጥፊያ፣ የመጋዘንና የክምችት ደህንነት መከታተያ ካሜራ፣ የክምችት እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያግዝ ሶፍትዌር እንደመጋዘኑ ነባራዊ ሁኔታ ይሟላል።

4/ Necessary materials for the Service's warehouse operations like forklifts, trolleys, pallets, backup power generators, temperature-and-humidity measuring devices, fire extinguishers, warehouse and stock-security monitoring cameras, software to assist in tracking stock movement, shall be provided according to the actual circumstances of the warehouse.

5/ የመጋዘን በሮች አስተማማኝነቱ በተረጋገጠ ቁልፍ መቆለፍ አለባቸው እንዲሁም ተገቢው ጥበቃ ሊደረግላቸዉ ይገባል፤ በተጨማሪም የመጋዘን ደህንነትን ለማጠናከር የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎችን ሊጠቀም ይችላል።

5/ Warehouse doors must be locked with locks of confirmed reliability and must be given appropriate guarding; in addition, technologies that help strengthen warehouse security may be used.

13. <u>የመድኃኒት ገቢ አደራረግ እና አመዘጋገብ ስርዓት</u>

13. <u>Pharmaceutical Receipt and Recording System</u>

1/ በአገልግሎቱ የኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እና መድሃኒት ወደ አገልግሎቱ መጋዘን በሚያመጡ ሌሎች ድርጅቶች በሚደርስ የቅድመ ጭነት መረጃ መሰረት ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ

1/ Based on pre-shipment information received from the Service's Contract Management Directorate and other organizations bringing pharmaceuticals to the Service's warehouse, appropriate

የመረከቢያ ስፍራ ማዘጋጀትና አስፈላጊውን ግብዓት ማሟላት አለበት።

preparation must be made, the receiving area readied, and the necessary materials secured.

2/ ማንኛዉም ወደ አገልግሎቱ መጋዘን ገቢ የሚደረግ መድሃኒት በአገልግሎቱ ኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በኩል የመድሃኒት ገቢ ማድረጊያ ማዘዣ ቁጥር ይዘጋጃል።

2/ For any pharmaceuticals to be received into the Service's warehouse, a pharmaceutical inbound delivery Number shall be prepared through the Service's Contract Management Directorate.

3/ በባህር ትራንስፖርት የሚገቡ መድኃኒቶችን በተመለከተ የመጋዘን ኃላፊው የጭነት ሰነዱን መረጃ ከኮንቴይነሩ እና ከቁልፍ ሚስጥር ቁጥሮች ጋር በማመሳከር ጭነቱ የአገልግሎቱ መሆኑን አረጋግጦ ኮንቴይነሩ እንዲከፈት ያደርጋል።

3/ With respect to pharmaceuticals arriving by sea transport, the warehouse manager shall confirm, by cross-checking the shipping-document information against the container and seal numbers, that the products belong to the Service, and shall then have the container opened.

4/ በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (3) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮንቴይነሩ ወደብ ላይ ለፍተሻ ተከፍቶ በድጋሚ በተንጠልጣይ ቁልፍ ተቆልፎ ከሆነ የመክፈቻ ቁልፉ በፖስታ ታሽጎ የጉምሩክ ማህተም መደረጉ ተረጋግጦ ይከፈታል።

4/ Sub-article (3) of this Article, where the container has been opened for inspection at the port and re-locked with a padlock, it shall be opened once it is confirmed that the key has been sealed in an envelope bearing the customs seal.

5/ መድሃኒቶች በርክክብ ወቅት የመድሃኒቱ አይነት፣ መጠን ፣ የሽረት ጊዜ፣ አምራች፣ አስተሻሸግ፣ አካላዊ ሁኔታ እና ሌሎች በእይታ ሊረጋገጡ የሚችሉ ሁኔታዎች መረጋገጥ አለባቸው።

5/ At the time of handover, the type, quantity, expiry date, manufacturer, packaging, physical condition, and other visually verifiable conditions of the Pharmaceuticals must be confirmed.

6/ ማንኛዉም በአየርም ይሁን በየብስ ተጓጉዞ የመጣ መድሃኒት ወደ አገልግሎቱ መጋዘን በሚገባበት ጊዜ የመጋዘን ኃላፊው የሸያጭ ደረሰኝ እና የመድሃኒት ዝርዝር መግለጫ ላይ ባለው መረጃ መሰረት ከአስረካቢው ጋር ርክክብ ይፈፀማል።

6/ When any Pharmaceuticals transported by air or by land arrives at the Service's warehouse, the warehouse manager shall carry out handover with the deliverer based on the information in the Commercial invoice and the packing list.

7/ ወደ አገልግሎቱ መጋዘን የደረሰ ማንኛውም ጭነት ወደ መጋዘን የደረሰበት ቀን፣ የመድኃኒቱን መግለጫ፤ ጥቅል ብዛት፣ ጭነቱን ያመጣው ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር፣

7/ Any shipment arriving at the Service's warehouse must be recorded on receipt of incoming goods containing the date of arrival, the description of the Pharmaceutical, the total number of packages,

የአስረካቢው ስምና አድራሻ በያዘ የገቢ መመዝገቢያ ሰነድ ላይ መመዝገብ አለበት።

the plate number of the vehicle that brought the consignment, and the deliverer's name and address.

8/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) በተገለጸዉ አግባብ ርክክብ ሲደረግ ልዩነት ካለ በትክክል የደረሰው መጠን ብቻ ገቢ ተደርጎ ልዩነቱ በጉድለት ወይም በብልጫ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ላይ ተሞልቶ አስረካቢው፣ ተረካቢው እና የመጋዘን አስተዳደር ቡድን መሪ ወይም የክፍሉ ዳይሬክተር ከፈረሙበትና ማህተም ከተደረገበት በኋላ ቅጂው ለአገልግሎቱ ኮንትራት አስተዳድር ዳይሬክቶሬት ወይም ለአምጪው አካል እንዲደርሰው ይደረጋል።

8/ Where a discrepancy exists at the time of handover under sub-article (6) of this Article, only the physical quantity actually received shall be recorded as received, and the discrepancy shall be recorded on a shortage-or-overage report form, signed by the deliverer, the recipient, and the warehouse management team leader or the department director, after which a copy shall be sent to the Service's Contract management Directorate or to the deliverer.

9/ ከአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት ወይም ከአቅራቢ የተጓዝዘ መድሃኒት ርክክቡ በቅርንጫፍ በሚሆንበት ጊዜ ልዩነት ካለ ልዩነቱ በጉድለት ወይም ብልጫ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ላይ ተሞልቶ አስረካቢው፣ ተረካቢው እና የሚመለከተው ኃላፊ ከፈረመበትና ማህተም ከተደረገበት በኋላ ቅጂው ለመጋዘን እና ለስርጭት አስተዳደር የስራ ክፍሎች እንዲደርሳቸው ይደርጋል።

9/ When the handover of Pharmaceuticals delivered from the Service's Head Office or from a supplier takes place at a Branch and a discrepancy exists, it shall be recorded on a shortage-overage report form, signed by the deliverer, the recipient, and the respective official, after which a copy shall be forwarded to the warehouse and distribution management units.

10/ በርክክብ ጊዜ ተሰብሮ ወይም ተበላሽቶ የተገኘ መድሃኒት በመለየት መጋዘን የደረሰውን መድሃኒት የመድሃኒት ሽያጭ ደረሰኝ እና የመድሃኒት ዝርዝር መግለጫ እንዲመሳከር ከተደረገ በኋላ ለቀጣይ እርምጃ ወደ ለአገልግሎቱ ኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ይደረጋል።

10/ Pharmaceuticals found broken or damaged at the time of handovering shall be sorted, and cross checked against the commercial invoice and packing list that arrived at the warehouse, shall be reported to the Service's Contract management Directorate for further action.

11/ መድሃኒቱ በተገቢው ሁኔታ ከተለየና ከአስረካቢው ጋር ርክክብ ከተፈፀመ በኋላ የመድሃኒት ገቢ ማድረጊያ ማዘዣ ቁጥር ከተመዘገበው መረጃ ጋር በማመሳከር የመድሃኒቱን መረጃ ወደ ተቋሙ መረጃ ቋት

11/ Once the Pharmaceutical has been properly sorted and handovering with the deliverer is completed, the inbound delivery number shall be cross-checked against the registered information, the Pharmaceutical's information entered into the system, and a goods-receipt voucher prepared.

ገቢ በማድረግ የገቢ ማረጋገጫ ሰነድ ይዘጋጃል።

12/ ወደ መጋዘን የገባ መድኃኒት በዓይነቱና በመለያ ቁጥሩ ተለይቶ ይቀመጣል።

13/ ከፍተኛ ክብደት ያላቸውና መደርደሪያ ላይ ለማስቀመጥ አመቺ ያልሆኑ መድኃኒቶች ደህንነታቸው ተጠብቆ በፓሌት ሆኖ መሬት ላይ ወይም በታችኛው መደርደሪያ ላይ መቀመጥ ይኖርባቸዋል።

14/ በማከማቻ መጋዘን ያለው መደርደሪያ በቂ ካልሆነ መድኃኒት ለማከማቻ በተዘጋጀ ቦታ ላይ በባች እና በሽረት ጊዜ ተለይቶ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በፓሌት ተደርጎ ይቀመጣል።

15/ የክትባት መድኃኒቶች ወደ መጋዘን እንደገቡ የክትባት መድረስ ማረጋገጫ ሰነድ ተሞልቶ ለሚመለከታቸዉ አካላት ይላካል።

16/ ወደ ማዕከላዊ መጋዘን ገቢ የሚደረጉና ፍተሻ የሚያስፈልገው የህክምና መሳሪያ መረከቢያ መጋዘን እንደደረሰ በህክምና መሳሪያ ባለሙያ፣ የአቅራቢው ወኪል እንዲሁም የመጋዘን ተረካቢ ባለሙያ ባለበት በግዥ ትዕዛዝ መስፈርት መሰረት ተፈትሾ በፍተሻዉ ውጤት መሰረት ገቢ ይደረጋል፤ ልዩነት ካለ በአገልግሎቱ ኮንትራት አስተዳደር ዳሬክቶሬት በኩል እንዲያስተካክል አቅራቢው እንዲያውቀው ይደረጋል።

17/ ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፎች፣ ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፍ፣ ከቅርንጫፍ ወደ ዋናው መስሪያ ቤት እንዲሁም ከመጋዘን ወደ መጋዘን የሚላኩ መድሃኒቶች ከላኪው አካል በሚዘጋጀው የክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ

12/ Pharmaceuticals received into the warehouse shall be sorted and stored by type and batch number.

13/ Pharmaceuticals of high load that are not convenient to store on upper racks must be kept safely on the floor by the pallets or on the lowest racks.

14/ When racks in the storage warehouse is insufficient, Pharmaceuticals shall be safely stored on pallets, sorted by batch and expiry date, in a designated storage area.

15/ When vaccines are received into the warehouse, a vaccine-arrival report shall be completed and sent to the relevant bodies.

16/ Medical device received into the central warehouse that requires inspection shall be inspected against the purchase order specifications in the presence of the bio- medical professional, the supplier's representative, and the receiving warehouse professional upon arrival at the receiving warehouse, and shall be received in accordance with the inspection result; where a discrepancy exists, the supplier shall be notified, through the Service's Contract Administration Directorate, to make the necessary correction.

17/ Pharmaceuticals sent from the Head Office to Branches, from a Branch to another Branch, from a Branch to the Head Office, or from one warehouse to another, shall be received on the basis of a Goods -receiving Voucher, in

መሰረት በመድሃኒት መረከቢያ ሰነድ ገቢ ይደረጋል።

accordance with the stock-transfer Vouturet prepared by the dispatching body.

18/ ከጤና ተቋማት ወይም ከሌላ ድርጅት ተመላሽ የሚደረግ መድኃኒት በተመላሽ የመድሃኒት መረከቢያ ሰነድ ገቢ ይደረጋል።

18/ Pharmaceuticals returned from health facilitys or another organization shall be received by a Stock Return Memo.

19/ በተቆጣጣሪ አካል የጥራት ፍተሻ ያልጨረሰና ከጥራት ጋር በተያያዘ እንዳይሰራጭ የተደረገ መድሃኒት የጥራት ፍተሻ ውጤት እስኪረጋገጥ ድረስ የጥራት ፍተሻ ላይ ያለ የክምችት አይነት በሚል መመዝገብና በመጋዘን ውስጥ በተለየ ስፍራ ይቀመጣል።

19/ Pharmaceuticals whose quality inspection by the Regulatory Body has not been completed, and which has consequently been withheld from distribution, shall be registered as stock pending quality inspection and kept in a designated area of the warehouse until the quality inspection result is confirmed.

20/ በተረጋገጠ የጥራት ችግር ምክንያት ከደንበኛ የተመለሰ ወይም እንዳይሰራጭ የተደረገ፣ በክምችት ወቅት የተበላሸ እንዲሁም በተለያየ ምክንያት የኢንሹራንስ ጥያቄ የቀረበበት መድሃኒት ተገቢው ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የተገደበ የክምችት አይነት በሚል ተመዝግቦና አስፈላጊው ምልክት ተለጥፎበት በመጋዘን ውስጥ በተለየ ስፍራ ይቀመጣል፣ ዝርዝር መረጃዉ ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ እንዲያውቀው ይደረጋል።

20/ Pharmaceuticals returned from a customer due to a confirmed quality problem, withheld from distribution, damaged during storage, or subject to an insurance claim for various reasons shall, pending an appropriate decision, be recorded as a blocked stock category, labeled with the necessary markings, and stored in a separate location within the warehouse; detailed information thereof shall be brought to the attention of the relevant senior official.

21/ በአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት መጋዘን ሳይራገፍ በቀጥታ ወደ ቅርንጫፍ ወይንም በአገልግሎቱ ቅርንጫፍ መጋዘን ሳይራገፍ በቀጥታ ወደ ጤና ተቋም በሚሰራጭበት ወቅት የገቢ ወጪ ሰነድ ተሰርቶ ከጭነቱ ጋር ወደ ተቀባዩ ይላካል።

21/ When pharmaceuticals is distributed directly to a Branch without being unloaded at the Head Office warehouse, or directly to a health facility without being unloaded at the Branch warehouse, a goods-receipt/issue document shall be prepared and sent to the recipient together with the consignment.

22/ ከአቅራቢ በቀጥታ ወደ አገልግሎቱ ቅርንጫፍ ወይም ጤና ተቋም የተላኩ መድሃኒቶች መድረሳቸውን የአገልግሎቱ ቅርንጫፍ ወይም ጤና ተቋሙ በደብዳቤ ሲያረጋግጥ የገቢ ወጪ ሰነድ ይሰራላቸዋል።

22/ When pharmaceuticals sent directly from a supplier to the Branches or a health facility, the goods receipt and issue document is prepared after the confirmation of the branch or the health facility by official letter.

14. <u>የቀዝቃዛ ሰንሰለት መጋዘን አስተዳደርና ክምችት ቁጥጥር</u>

1/ ማንኛውም ወደ ቀዝቃዛ ሰንሰለት መጋዘን የሚገባ የመጋዘን ሃላፊ ወይም ሰራተኛ የቅዝቃቅዜ መከላከያ ልብስ፣ ጓንት እና ሌሎች አስፈላጊ አልባሳትን መልበስ አለበት።

2/ በዋና መስሪያ ቤትና በቅርንጫፎች የሚገኝ የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጋዘን የቅዝቃዜ መጠኑ በቀን ሁለት ጊዜ ይመዘገባል።

3/ የቀዝቃዛ ሰንሰለት መጋዘንና ፍሪጅ የቅድመ ብልሽት ጥገና እቅድ ሊኖረውና ሊተገበር ይገባል።

4/ በአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት ወይም በቅርንጫፎች የሚገኙ መድሃኒት የሚቀመጥባቸው የቀዝቃዛ ሰንሰለት መጋዘኖች በየትኛውም ሰአት በብልሽት፣ በመብራት መጥፋት ወይም በሌላ ምክንያት ስራ ቢያቆሙ ወዲያውኑ ሊታወቅ የሚችልበትን ስርአት ይዘረጋል፤ እንዲሁም ጥገና ይከናወናል።

5/ በመብራት መጥፋትና በብልሽት ምክንያት የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጋዘኖችና ፍሪጆች መስራት ቢያቆሙ መጠባበቂያ ጀነሬተርና የሚተገበር የመጠባበቂያ እቅድ ይኖረዋል።

6/ አገልግሎቱ በቂ የሆነ የቅዝቃዜ ሰንሰለት መድሃኒቶችን ለማከማቸት የሚያገለግሉ የቀዝቃዛ ሰንሰለት መጋዘኖችና ፍሪጆች እንዲሁም በስርጭት ወቅት አገልግሎት ላይ የሚዉሉ በረዶዎችን ለማምረት የሚያገለግሉ ፍሪጆች ይኖሩታል።

7/ በደረቅ የመጋዘን አይነት ላይ የሚደረግ የመድሃኒት ቅበላ፣ የመድሃኒት ወጪ እና

14. <u>Cold Chain Warehouse Management and Inventory Control</u>

1/ The warehouse manager or any staff entering to the cold-chain warehouse must wear cold-protection clothes, gloves, and other necessary attire.

2/ The temperature of the cold-chain warehouse at the Head Office and Branches shall be recorded twice a day.

3/ The cold-chain warehouse and refrigerators shall have, and shall implement, a preventive-maintenance plan.

4/ The Cold-chain warehouses of the Head Office or Branches in which Pharmaceuticals is stored shall in place a system for immediate detection whenever operations cease at any time due to malfunction, power outage, or other causes, and maintenance shall be carried out accordingly.

5/ The contingency plan and backup generator shall be in place whenever the cold-chain warehouses and refrigerators cease operating due to power outage or malfunction.

6/ The Service shall have sufficient cold-chain warehouses and refrigerators for storing cold-chain Pharmaceuticals, as well as refrigerators for producing the ice packs used for coldchain pharmaceuticals distribution.

7/ The pharmaceutical receipt, issuance, and stock-control operations carried out for dry-storage

ክምችት ቁጥጥር ስራ ለቀዝቃዛ ሰንሰለት መጋዘንም ይሰራል።

warehouses shall likewise apply to the cold-chain warehouse.

15. የመድኃኒት ወጪ አደራረግ

1/ ከማከማቻ መጋዘን በሚዘጋጀው የመድሃኒት መሰብሰቢያ ሰነድ መሰረት ከተገቢው ቦታ፣ ትክክለኛውን መድኃኒት፣ መለያ ቁጥሩን መሰረት በማድረግ ከተሰበሰበ በኋላ ወደ ማስረከቢያ ስፍራ ይተላለፋል።

2/ ከማከማቻ ወደ ማስረከቢያ ስፍራ የተሰበሰበ መድኃኒት ወጪ ከመደረጉ በፊት፣ የክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ ተዘጋጅቶለት የመድሃኒቱ ዓይነት፣ መጠን፣ የሽረት ጊዜ፣ መለያ ቁጥር፣ አምራችና ይዘቱ ከሰነዱ ጋር መገናዘብ አለበት፤ ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላም ለጭነት ዝግጁ ይደረጋል።

3/ በቅርንጫፍም ይሁን በዋናዉ መስሪያ ቤት የፋብሪካ እሽግ ካርቶን አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ምስክሮች ባሉበት ተከፍቶ በውስጡ የተገኘዉ መጠን ፋብሪካዉ ከገለጸዉ መጠን ያነሰ ወይም የበለጠ ከሆነ ልዩነቱን በማረጋገጥና በመፈራረም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ይደረጋል።

4/ የመድኃኒት መውጫ ለተረከበው አካል የሚሰጠው በዋናው መስሪያ ቤት ከሆነ ከክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ ጋር በማመሳከር እንዲሁም በቅርንጫፎች ከሆን የእጅ በእጅ ሽያጭ ከሆነ ክፍያ መፈፀሙ ከተረጋገጠ በኋላ ሲሆን የዱቤ ሽያጭ ከሆነ የዱቤ ሽያጭ መመዝገቢያ ላይ ከተመዘገበ በኋላ ይሆናል።

15. Pharmaceutical Withdrawal Procedure

1/ After collection of pharmaceuticals by the picklist based on the location, batch number and other parameters, the pharmaceuticals shall be transferred to the dispatching area of the warehouse.

2/ Before Pharmaceuticals collected from storage to the dispatch area, a stock-transfer voucher shall be be prepared, and the verified against type, quantity, expiry date, batch number, manufacturer, and other parameters; once accuracy is confirmed and handover completed, it shall be made ready for loading.

3/ When a factory-sealed carton, at either a Branch or the Head Office, is found suspicious, it shall be opened in the presence of witnesses; if the quantity found inside is less or greater than that stated quantity by the manufacturer, the discrepancy shall be confirmed and counter signed, and reported to the Contract Management so that necessary action shall be taken.

4/ Pharmaceuticals gate pass shall be given at the Head Office by cross-checking against the stock transfer voucher and at Branches, in the case of a cash sale, after payment has been confirmed, and in the case of a credit sale, after the credit-sale after recorded on the credit sales registration

ንዑስ ክፍል ሁለት
የመድኃኒት ክምችት ቁጥጥር ስርዓት

Sub-Section Two
Pharmaceutical Inventory Control System

16. የመድኃኒቶች ክምችት ቆጠራ

1/ በአገልግሎቱ መጋዘን የሚገኙ መድኃኒቶች በመረጃ ቋትና በአካል የሚገኘው የክምችት ትክክለኛነት ለማረጋገጥና በመጋዘን አስተዳደር ኃላፊ በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት የክምችት ማስተካከያ ለማድረግ የክምችት ቆጠራ ይደረጋል።

2/ ኡደታዊ ቆጠራ አገልግሎቱ ዕቅድ አውጥቶ በየሩብ አመቱ የሚደርግ ቆጠራ ሆኖ የክምችትን ደህንነት ለመለየትና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ይደረጋል።

3/ አገልግሎቱ በመጋዘን ዉስጥ ያለ መድኃኒቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በተለያዩ ምክንያቶች እንዲቆጠርለት ሲፈልግ ኢመደበኛ ቆጠራ ይደረጋል።

4/ በአመታዊ፣ ኡደታዊ እና ኢመደበኛ ቆጠራ ወቅት የተገኙ ብልጫና ጉድለቶች፣ የመድሃኒት ክምችት ቆጠራ እና የቆጠራ ውጤት ማስተካከያዎች በአገልግሎቱ የንብረት ቆጠራ፣ ጉድለትና ብልጫ፣ ምዝገባ ማካካሻ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

17. ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው መድሃኒቶች አያያዝ እና ቁጥጥር

1/ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ ወይም በተለያየ ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ መድኃኒቶች አገልግሎት ከሚሰጡ መድኃኒቶች ተለይተውና መለያ ምልክት ተደርጎባቸው በተለየ መጋዘን

16. Pharmaceutical Stock Count

1/ An inventory count shall be conducted to verify the inventory accuracy between the system and the physical stock and to take appropriate corrective action as per the direction given by the warehouse management.

2/ A cyclical count is a count conducted by the Service, on the basis of a plan drawn up quarterly, in order to determine the safety of the inventory and confirm its accuracy.

3/ Where the Service wants the pharmaceuticals to be counted partially or fully due to different reasons, and ad-hoc counting shall be conducted.

4/ Overages and shortages found during annual, cyclical, and ad-hoc counts, and adjustments shall be handled in accordance with the Service's Property Count, Shortage and Overage, Registration and Adjustment Directive.

17. Handling and Control of Pharmaceuticals Requiring Special Care

1/ Pharmaceuticals that have expired, or are unusable for various reasons shall be separated from usable stock and labeled and stored in a separate warehouse or in a designated area within the same warehouse.

ውስጥ ወይም በተመሳሳይ መጋዘን ዉስጥ በተለየ ስፍራ ይከማቻሉ።

2/ በባህሪያቸው ተቀጣጣይ እና በቀላሉ እሳት የሚፈጥሩ ኬሚካሎች ለብቻቸው በተለየ መጋዘን ውስጥ ወይም በተመሳሳይ መጋዘን ዉስጥ በተለየ ስፍራ ይከማቻሉ።

3/ ልዩ ጥንቃቄ እና ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች በሚገኙበት መጋዘን ዉስጥ በተለየ ስፍራ ተቆልፎ ይከማቻል።

2/ Flammable and combustible chemicals shall be stored separately, either in a separate warehouse or in a designated area within the same warehouse.

3/ Narcotic and psychotropic Pharmaceuticals requiring special care and control shall be stored, locked, in a designated area within the warehouse in which they are stored.

18. <u>የተበላሹ መድኃኒቶች አስተዳደር</u>

1/ በመጋዘን ዉስጥ በስራ ሂደት ላይ የመድሃኒት ብልሽት ሲያጋጥም ከመጋዘን ሃላፊ በሚደርስ ሪፖርት መሰረት በመጋዘን አስተዳደርና ክምችት ቁጥጥር አስተባባሪ ተጣርቶ ለዳይሬክተር ወይም ለቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ሪፖርት ይደረጋል።

2/ በዚሁ አንቀፅ ንኡኡስ አንቀፅ (1) ላይ የተጠቀሰው ብልሽት ሲከሰት በሚደረገው ማጣራት መሰረት ለብልሽቱ ምክንያት ግዴለሽነትና ከጥንቃቄ ጉድለት ከሆነ ጥፋቱን ያደረሰው ሰራተኛ ማስረጃ ላይ ተመርኩዞ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ይወሰድበታል።

18. <u>Damaged Pharmaceuticals Management</u>

1/ When pharmaceutical damage occurs during operations within the warehouse, it shall be reported to the warehouse management director or the branch manager after the verification by the warehouse and inventory control management team leader based on the report that came from the warehouse manager.

2/ When the damage stated by this article sub-article (1) occurs, based on the investigation carried out, If the cause of the damage is due negligence or a lack of care, administrative and legal action shall be taken against the employee responsible for the fault, based on the evidence.

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የመድሃኒት ስርጭትና የተሽከርካሪ ስምሪት አስተዳደር</u>

19. <u>የመድሃኒት ስርጭት አስተዳደር</u>

<u>CHAPTER FOUR</u>

<u>PHARMACEUTICALS DISTRIBUTION AND FLEET MANAGEMENT</u>

19. <u>Pharmaceuticals Distribution Management</u>

የአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤትና ቅርንጫፎች የመድሃኒት ስርጭት አስተዳደር የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል፦

The Service's Head Office and Branches shall have the following duties and responsibilities:

1/ ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ የሚደረግ የመድኃኒት የስርጭት መርሐግብር ከፍላጎት አስተዳደር፣ ከመጋዘን ክትትል እና ከቅርንጫፍ ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል።

1/ The pharmaceutical distribution schedule from the Service head office to branch is prepared through coordination with demand management, warehouse operation management, and communication with the respective branches."

2/ ከፍላጎት አስተዳደር እና ከመጋዘን አስተዳደር ጋር በመነጋገር የጉዞ መስመርና የስርጭት መርሐግብር ያዘጋጃል፤ እንዲሁም መድሃኒት በቀጥታ ለሚቀርብለት ጤና ተቋም ወይም በወረዳ በኩል ለሚቀርብለት ጤና ተቋም የተዘጋጀውን የስርጭት መርሃ ግብር ለጤና ተቋም ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤት ያሳውቃል።

2/ In consultation with Demand Management and Warehouse Management, prepare the distribution route and schedule, and shall communicate the prepared distribution schedule to the respective health facilities (for direct delivery) or woreda health office (for non direct delivery),

3/ ከዋናው መስሪያ ቤት በቀጥታ ወደ ቅርንጫፍ ወይም ከቅርንጫፍ ወደ ጤና ተቋም ለሚሰራጭ መድኃኒት አስፈላጊውን መረጃ ከክምችት አስተዳደር ጋር በመነጋገርና ከመጋዘን አስተዳደር በመረከብ የስርጭት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ እንዲሰራጭ ይደረጋል።

3/ For Pharmaceutical to be distributed directly from the Head Office to a Branch, or from a Branch to a health facility, the necessary information shall be obtained in consultation with inventory management and received from Warehouse management, a distribution schedule prepared, and distribution carried out accordingly.

4/ በአየር ተጓጉዞ አየር ማረፊያ ለሚደርስ መድሃኒት ከኮንትራት አስተዳደር በሚመጣ ጥያቄ እና መድኃኒት ገቢ ማድረጊያ ማዘዣ ቁጥር መሰረት አስፈላጊውን ተሽከርካሪ በመመደብ መድሃኒቶች በወቅቱ ወደ ሚፈለገው መጋዘን ወይም የቅዝቃዜ ክፍል እንዲገባ ይደረጋል።

4/ For Pharmaceutical arriving by air transport at an airport, based on a request from Contract management and the pharmaceuticals goods-receipt voucher number, a suitable vehicle shall be assigned so that the Pharmaceuticals reach the required warehouse or cold room in time.

5/ ከመደበኛ የስርጭት መርሃ ግብር ውጭ ከዋና መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ ወይም ወደ ጤና ተቋም ለድንገተኛ አገልግሎት፣ ለወረርሽኝ የሚውል መድሃኒት ማሰራጨት በሚያስፈልግበት ጊዜ ከሚመለከተው የስራ

5/ Where it becomes necessary to distribute Pharmaceutical, outside the regular distribution schedule, from the Head Office to a Branch or health facility for emergency or epidemic use, shall, in consultation with the relevant Service's

ኃላፊ ጋር በመነጋገር የመደበኛውን የስርጭት ስርዓት ሳይጠብቅ እንደ አስፈላጊነቱ በፍጥነት ያሰራጫል።

head, distribute it promptly as necessary, without adhering to the regular distribution system.

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ለተገለፀው ስርጭት የገቢ እና የስርጭት ሰነድ ተዘጋጅቶለት በተገቢው ሁኔታ ስለ መሰራጨቱ በሰነድ መረጋገጥ ይኖርበታል።

6/ For the distribution referred to in sub-article (5) of this Article, a receipt-and-distribution document shall be prepared, and the distribution must be duly confirmed by documentation.

7/ መድሃኒትን ክሮስ ዶክ ማድረግ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ከመድሃኒት አቅራቢ በቀጥታ ወደ ቅርንጫፍ ወይም ጤና ተቋም እንዲሁም ከአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት ወደ ጤና ተቋም አስቀድሞ በማሳወቅና አስፈላጊውን ሰነድ በማሟላት በቀጥታ እንዲሰራጭ ይደረጋል።

7/ Where it becomes necessary to cross-dock Pharmaceutical, it shall, by giving prior notice and completing the necessary documentation, be distributed directly from the pharmaceutical supplier to a Branch or health facility, or from the Service's Head Office to a health facility.

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ መድሃኒቱ ክሮስ ዶክ ከተደረገ በኋላ አስፈላጊው ማረጋገጫ ከተረካቢው አካል ሲደርስ የገቢ ወጭ ሰነድ መሰራት ይኖርበታል።

8/Notwithstanding sub-article (7) of this Article, once the Pharmaceutical has been cross-docked as necessary, a goods-receipt/issue document shall be prepared once the necessary confirmation is received from the recipient body.

9/ የቅዝቃዜ ሰንሰለት ለሚያስፈልገው መድሃኒት ከአየር መንገድ ወደ ዋናው መስሪያ ቤት፣ ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ እንዲሁም ከቅርንጫፍ ወደ ጤና ተቋም በሚጓጓዙበት ጊዜ ተገቢውን የቅዝቃዜ ሰንሰለት ጠብቆ መጓጓዝ ይኖርበታል።

9/ Medicine requiring a cold chain must be transported while maintaining the appropriate cold chain when moved from the airline to the Head Office, from the Head Office to a Branch, and from a Branch to a health facility.

10/ ልዩ ባህሪ ያለው መድሃኒት እንደየ ባህሪው አስፈላጊው ተሸከርካሪ ተመድቦ ክትትልና ጥንቃቄ እየተደረገ እንዲጓጓዝ ይደረጋል።

10/ Pharmaceuticals with special characteristics shall, depending on its characteristics, be transported using an appropriately assigned vehicle, with ongoing monitoring and care.

20. <u>የመድኃኒት አላላክ እና ርክክብ ስርዓት</u>

20. <u>Pharmaceutical Dispatch and Handover System</u>

1/ ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ፣ በቅርንጫፎች መካከል፣ ከቅርንጫፍ ወደ ዋናው መስሪያ ቤት የሚላክ መድኃኒት ርክክብ

1/ Handover of Pharmaceutical sent from the Head Office to a Branch, between Branches, or from a Branch to the Head Office shall be carried out by the

የሚፈፀመው ተረካቢው እና አስረካቢው መድኃኒቱን በመቁጠርና ከተዘጋጀው ሰነድ ጋር በማመሳከር በመረካከቢያ ሰነዶች ላይ በመፈራረም ይረካከባሉ።

recipient and the deliverer counting the Pharmaceutical, cross-checking it against the prepared document, and signing the handover documents.

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላኪው ዋናው መስሪያ ቤት ወይም ቅርንጫፍ ኦርጂናል እና ኮፒ የክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ ለተረካቢው መላክ አለበት፤ ተረካቢው ርክክቡ ካለቀ በኋላ ኦርጅናሉን በማስቀረት ኮፒው ላይና የመድሃኒት ገቢ ማረጋገጫ ሰነድ በመቁረጥ ፊርማና ማህተም በማድረግ ባስረካቢው በኩል ለላኪው እንዲደርስ ያደርጋል።

2/ Under sub-article (1) of this Article, the dispatching Head Office or Branch must send the original and a copy of the stock-transfer document to the recipient; once handover is completed, the recipient shall retain the original, issue pharmaceutical-receipt confirmation document on the copy, sign and seal it, and have it returned to the sender through the deliverer.

3/ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም እንደአስፈላጊነቱ በአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊ አቅጣጫ መሰረት የጊዜያዊ የክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ እንደ ክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ ይጠቀማል።

3/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, where an unavoidable situation arises, a temporary stock-transfer document/manual delivery note shall, as necessary, be used as the stock-transfer document, in accordance with the direction of the head of the Service.

4/ ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ፣ ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፍ ወይም ወደ ዋናው መስሪያ ቤት መጋዘን መድሃኒቱ ደርሶ የክምችት መረከቢያ ደረሰኝ በሲስተምና በሌሎች ምክንያቶች ሳይቆረጥ ሲቀር የክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ እና የገቢ ማድረጊያ ማዘዣ ቁጥር ተጠቅሶ ተረካቢው መጋዘን ስለመረከቡ ህጋዊ ደብዳቤ ለአስረካቢው በመስጠት የገቢ ማረጋገጫ ደረሰኝ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መላክ ይኖርበታል።

4/ Where Pharmaceutical has arrived at the Head Office, at another Branch, or at the Head Office warehouse from a Branch, but the stock-receiving voucher has not been generated due to system or other reasons, the recipient warehouse shall issue the deliverer a formal letter confirming receipt, citing the Stock Transfer Voucher and the Goods-receiving number; the recipient shall then be required to send the Goods Receiving Voucher within one week.

5/ በርክክብ ወቅት በዋናው መስሪያ ቤት ወይም በቅርንጫፍ መጋዘን በደረሰው ብዛትና በክምችት ማስተላለፊያ ወይም በጊዜያዊ የክምችት ማስተላለፊያ ሰነድ መካከል፤

5/ Where, at the time of handover, a discrepancy exists between the quantity arriving at the Head Office or Branch warehouse and the stock-transfer document or temporary stock-transfer document:

ሀ) ብልጫ በሚኖርበት ጊዜ ተረካቢው በሰነዱ የተጠቀሰውን መጠን ተረክቦ ለተፈጠረው ብልጫ ከሚመለከተው ባለሙያ እና የስራ ኃላፊ ጋር ምክንያቱን በማጣራት ብልጫውን በእለቱ በደብዳቤ ለላኪው አካል ያሳውቃል።

(a) Where there is an overage, the recipient shall receive the quantity stated in the document, investigate the cause of the overage together with the relevant professional and head of operations, and notify the dispatching body of the overage, in letter, on the same day.

ለ) ጉድለት በሚኖርበት ጊዜ ተረካቢው መድሃኒቱን ሳይረከብ ለተፈጠረው ጉድለት ከሚመለከተው ባለሙያ እና የስራ ኃላፊ ጋር በመነጋገር ምክንያቱ እንዲጣራ እና ውሳኔ እንዲሰጥበት በደብዳቤ ለላኪው አካል ያሳውቃል።

(b) In the case of a shortage, the receiving party shall, without accepting the pharmaceuticals, consult with the relevant professional and work supervisor and notify the dispatching party in writing so that the reason may be verified and a decision rendered.

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ላይ የተጠቀሱት ልዩነቶች ሲያጋጥሙ የመድሃኒት ስርጭት ክፍል በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለቅርንጫፉ ያሳውቃል።

6/ Where the discrepancies referred to in sub-article (5) of this Article occur, the Pharmaceutical Distribution Division shall render a decision within five consecutive working days and notify the branch.

7/ መድኃኒት ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ በሚጓጓዝበት ወቅት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ተሰብሮ ወይም ተበላሽቶ ወደ መረከቢያ መጋዘን የደረሰ ከሆነ ተረካቢው ቅርንጫፍ የጉዳቱን መንስኤ፣ አይነት እና መጠን አጣርቶ በመመዝገብ ለስርጭትና ተሽከርካሪ ስምሪት ክፍል በደብዳቤ ያሳውቃል።

7/ When Pharmaceutical transported from the Head Office to a Branch arrives at the receiving warehouse partially or wholly broken or damaged, the recipient Branch shall investigate and record the cause, type, and extent of the damage, and notify the Distribution and fleet management unit by letter.

8/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (7) የተገለፀው ሲያጋጥም ከቅርንጫፍ በመጣ ሪፖርት መሰረት የስርጭት ክፍል ክትትል በማድረግ ለተረካቢው ቅርንጫፍ ውሳኔውን በሁለት ቀናት ውስጥ ያሳውቃል።

8/ Where the circumstance described in sub-article (7) of this Article occurs, the Distribution Team shall follow up based on the report received from the branch and notify the receiving branch of its decision within two days.

9/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) (ለ) እና (7) የተጠቀሰው ሲያጋጥም የስርጭት ክፍል እንደ አስፈላጊነቱ በወቅቱ ውሳኔ በመስጠት ወይም እንዲሰጥበት ለሰው ኃብት አስተዳደር፣

9/ Where the matters referred to in sub-articles (5)(b) and (7) of this Article occur, the Distribution Team shall, as necessary, either render a timely decision itself or notify the Human Resource

ለፋይናንስ ክፍል ወይም ለበላይ ኃላፊ በማሳወቅ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል።

Administration, the Finance Division, or the higher official so that a decision may be rendered.

10/ በስርጭት ወይም በማጓጓዝ ሂደት ላይ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት በሚደርስ ጉዳት መድሃኒቱን የሚያጓጉዘው አካል ለመድሃኒት ስርጭትና ተሽከርካሪ ስምሪት ክፍል ያሳውቃል።

10/ Where damage occurs during distribution or transport, whether man-made or natural, the body transporting the Pharmaceutical shall notify the Pharmaceutical Distribution and fleet management unit.

11/ መድኃኒት ከስርጭት በኋላ የጥራት ጉድለት እንዳለው ወይም ጥራቱ አጠራጣሪ እንደሆነ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ እና ወደ ተሰራጨበት መመለስ ሲያስፈልግ ወይም ለክፍሉ ጥያቄ ሲቀርብ መድኃኒቱ እንዲሰበሰብ ተሽከርካሪ በመመደብ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ እንዲመለስ ይደረጋል።

11/ Where it is confirmed by the relevant body that Pharmaceutical has a quality defect, or that its quality is questionable, after distribution, and it becomes necessary to return it, or a request is submitted to the unit, a vehicle shall be assigned to collect the Pharmaceutical and it shall be returned with the necessary care.

12/ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5፣ 6 እና 8) እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያጋጥሙ ብልጫና ጉድለቶች በአገልግሎቱ የፋይናንስ መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል።

12/ Subject to the provisions of Sub-Articles (5), (6), and (8) of this Article, any surpluses or shortages that may arise shall be addressed in accordance with the financial management directive of the Service

13/ በተለያዩ ምክንያት ሊወገድ የተዘጋጀ መድኃኒት እንዲጫን እና እንዲወገድ ከሚመለከተው አካል በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት አስፈላጊውን ተሽከርካሪ በመመደብ እና ርክክብ በመፈጸም ወደ ጥቅም ላይ የማይውሉ መድሃኒቶች ማስወገጃ ማዕከል እንዲጓጓዝ በማድረግ የገቢ ማረጋገጫ ሰነድ ይሰበስባል።

13/ Based on a request submitted by the relevant body regarding Pharmaceutical prepared for disposal for various reasons, the unit shall assign the necessary vehicle, complete handover, cause it to be transported to the disposal center for unusable Pharmaceuticals, and collect the Goods Receiving Voucher.

21. <u>ለጤና ተቋም የሚደረግ የመድኃኒት ስርጭትን በተመለከተ</u>

21. <u>Regarding Pharmaceutical Distribution to Health Facility</u>

1/ ከቅርንጫፍ ወደ ጤና ተቋም የሚላክ መድኃኒት ርክክብ የሚፈፀመው ተረካቢው እና አስረካቢው በሰነዱ የተጠቀሰውና በአካል

1/ Handover of Pharmaceuticals sent from a branch to a health facility shall be carried out by the recipient and the deliverer, after counting and

የደረሰውን ቆጥረው ካረጋገጡ በኋላ በመፈራረም ይሆናል፤ ተረካቢው ጤና ተቋምም ሞዴል 19 በመቁረጥ ወይም የገቢ ማረጋገጫ ደረሰኝ እና የተቋሙን ማህተም በማድረግ ላስረካቢው ይሰጣል፤ አስረካቢውም ሞዴል 19 ኙን ከመስክ እንደተመለሰ ወዲያውኑ ለክፍሉ ያስረክባል።

confirming the quantity stated in the document against what physically arrived, by signing; the recipient health facility shall issue a Model 19 or Goods receipt, affix the facility's seal, and give it to the deliverer, who shall hand it over to the unit immediately upon returning from the field.

2/ በርክክብ ወቅት ጤና ተቋም በደረሰው ብዛትና በሰነዱ ላይ በተገለፀው መካከል በማነስ ወይም በመብለጥ ልዩነት በሚከሰትበት ጊዜ ተረካቢው ጤና ተቋም ወይም ወረዳ ጤና ፅህፈት ቤት በተረከባቸው መድኃኒቶችና በተላከለት ደረሰኝ መካከል ያለውን ልዩነት በመግለጽ ልዩነቱን የሚያሳይ የገቢ ማረጋገጫ ሰነድ አስረካቢው ለላኪዉ ማምጣት ይኖርበታል።

2/ Where, at the time of handover, a discrepancy, whether a shortage or a surplus, arises between the quantity received by the health facility and the quantity stated in the document, the receiving health facility or woreda health office shall specify the discrepancy between the pharmaceuticals received and the dispatch receipt sent to it, and shall deliver to the sender a goods receipt confirmation document showing the discrepancy.

3/ በዚሁ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (2) የተገለጸው ልዩነት በብልጫ ከሆነ መድሃኒቱ ወደ አገልግሎቱ ቅርንጫፍ መጋዘን ተመላሽ ይደረጋል እንዲሁም ልዩነቱ የጉድለት ከሆነ ለተገኘው ጉድለት በኃላፊነት የሚጠየቅ አካል ካለ በመለየት ለስርጭት አስተባባሪው ከቀረበ በኋላ የውሳኔ ሀሳብ ለቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ መቅረብ አለበት።

3/ Where the discrepancy referred to in sub-article (2) of this Article is an overage, the Pharmaceutical shall be returned to the Service’s Branch warehouse; where the discrepancy is a shortage, any body to be held responsible shall be identified, submitted to the Distribution Coordinator, and a recommendation for decision submitted to the Branch Manager.

4/ ጤና ተቋም ወይም ወረዳ ጤና ፅህፈት ቤት የተላከለትን መድኃኒት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመመለስ አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር አስረካቢው ለቅርብ ኃላፊው በማሳወቅ ለአስረከባቸው መድሃኒቶች ብቻ የገቢ ማረጋገጫ ሰነድ በማምጣት ተመላሽ ለሚደረግ መድሃኒት በልዩነት መመለሻ ሰነድ ወደ አገልግሎቱ ቅርንጫፍ መጋዘን ተመላሽ ይደረጋል።

4/ Where a compelling circumstance arises requiring the health facility or woreda health office to return, wholly or in part, pharmaceuticals sent to it, the receiving party shall notify its immediate supervisor, deliver a goods receipt confirmation document only for the pharmaceuticals it has accepted, and the pharmaceuticals to be returned shall be sent back to the Service's branch warehouse using a discrepancy return document.

5/ ከአገልግሎቱ ጋር ውል ተገብቶ በቀጥታ ለጤና ተቋም የሚደረገው የተገላባጭ ፈንድ መድኃኒት ርክክብ በሚፈፀምበት ጊዜ የዱቤ ሽያጭ ሰነዱ ላይ ተረካቢው ከፈረመ በኋላ የተቋሙ ማህተም ተደርጎበት፣ የገቢ ሰነድ (ሞዴል 19) ተቆርጦለት፣ የሰነድ ቁጥሩ ተጠቅሶ ጤና ተቋሙ መረከቡን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ መሰጠት አለበት።

5/ When handover of revolving-fund Pharmaceutical supplied directly to a health facility under an agreement with the Service is carried out, once the recipient has signed the credit-sale document, the facility's seal shall be affixed, a receipt document (Model 19) issue , and a letter confirming receipt by the health facility, citing the document number, shall be given.

22. ጤና ተቋም ወደ አገልግሎቱ ቅርንጫፍ መጥተው መድኃኒት የሚረከቡበት ሁኔታ

22. Circumstances under which a Health facility Comes to the Service's Branch to Receive Medicine

1/ ጤና ተቋም በፍጆታ መጨመር፣ በወረርሽኝ ወይም በሌላ አስገዳጅ ሁኔታ ወደ አገልግሎቱ ቅርንጫፍ መጥቶ መድሃኒት እንዲረከብ ሲያስፈልግ ጤና ተቋሙ ውክልና በሰጠው ባለሙያ መድሃኒቱን ይረከባል፤ እንዲሁም ለሚረከበው መድኃኒት ሙሉ ሃላፊነት ይወስዳል።

1/ Where, due to an increase in consumption, an epidemic, or another compelling circumstance, a health facility needs to come to the Service's Branch to receive Pharmaceutical, the delegated by the health facility shall receive the Pharmaceutical and shall assume full responsibility for it.

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በተጠቀሰው መሰረት መድኃኒቱ በትክክል መድረሱን የሚያረጋግጥ ሞዴል 19 ወይም የገቢ ማድረጊያ ሰነድ በ ሰባት (7) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ዉስጥ መላክ ይኖርበታል።

2/ Under sub-article (1) of this Article, a Model 19 or Goods Receiving Voucher that the Pharmaceutical has properly arrived must be sent within seven (7) consecutive days.

23. የተሽከርካሪ ስምሪት አስተዳደር

23. Fleet Deployment Management

የአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤትና ቅርንጫፎች የመድሃኒት ስርጭት ክፍል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፦

The Pharmaceutical Distribution unit of the Service's Head Office and Branches shall, have the following main duties and responsibilities:

1/ ለስምሪት ዝግጁ የሆነ ተሽከርካሪ በስምሪት ባለሙያና በክፍሉ አስተባባሪ በአይነትና በቁጥር እንዲሁም የአሽከርካሪ እና የረዳት ስም ለይቶ የማወቅና የመያዝ፤

1/ Vehicles ready for dispatch must be identified and recorded, by type and number, by the transportation officers and the unit coordinator, together with the names of the driver and assistant.

2/ ለመድሃኒት ስርጭት፣ ለቢሮ ወይም ለመስክ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪ ከስምሪት በፊትና በኋላ መነሻና መድረሻ ኪሎ ሜትር በመመዝገቢያ ቅጽ ላይ የመመዝገብ፤

2/ For vehicles used for pharmaceutical distribution, office, or field service, the starting and ending kilometers/mileage must be recorded on a registration form before and after dispatch.

3/ ለመድሃኒት ስርጭት ተሽከርካሪ በሚመደብበት ወቅት የጉዞ መስመሩን፣ የመድሃኒቱን አይነት፣ ባህሪ፣ ክብደትና ይዘት መረጃ መሰረት የማድረግ፤

3/ When a vehicle is assigned for pharmaceutical distribution, it shall be based on the distribution route and on information as to the type, characteristics, weight, and content of the product.

4/ የአገልግሎቱ ተሽከርካሪ የስርጭቱን ፍላጎት የማይሸፍን ከሆነ በኮንትራት ውል ከተገባላቸው ከግል የትራንስፖርት አቅራቢ በአይነትና በመጠን አስፈላጊ የሆነ ተሽከርካሪ ለይቶ የማቅረብ፤

4/ Where the Service's vehicles do not cover the distribution need, the unit shall cause the necessary vehicle, by type and quantity, to be supplied from a private transport provider engaged under a contractual agreement.

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተገለጸው መሰረት ለጭነት ለሚቀርብ ተሽከርካሪ በአይነትና በመጫን አቅም በውሉ በተቀመጠው ስምምነት መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ፤

5/ It shall confirm that a vehicle supplied for freight under sub-article (3) of this Article conforms, as to type and loading capacity, to the agreement set out in the contract.

6/ በኪራይ መኪና ለሚጓጓዝ መድሃኒት የመጓጓዣ ክፍያ መጠየቂያ ሲቀርብ አስፈላጊውን ሰነድ ትክክለኛነቱን በማጣራት እና በማረጋገጥ ለፋይናንስ የስራ ክፍል የማቅረብ፤

6/ Where a transport-payment claim is submitted for Pharmaceutical transported by a rented vehicle, the unit shall verify and confirm the accuracy of the necessary documents and submit it to the Finance unit.

7/ ማንኛውም ተሽከርካሪ ስምሪት ተሰጥቶት በሚጓጓዙበት ጊዜ ተሽከርካሪው እና የተጫነው መድሃኒት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ፤

7/ Whenever the vehicle is dispatched and in transit, the unit must exercise the necessary monitoring so that the security of the vehicle and the Pharmaceutical shipped is maintained.

8/ በአገልግሎቱ ለሚገኝ ማንኛውም ተሽከርካሪ ክትትል በማድረግ መደበኛ ወይም ቅድመ ብልሽት ጥገና ወቅቱን ጠብቆ የሚደረግለት መሆኑን ማረጋገጥ።

8/ Any vehicle belonging to the Service shall be monitored, and regular or preventive maintenance shall be carried out for it in a timely manner.

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

24. ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያ

በአገልግሎቱ ዋና መስሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ የመድሃኒት ፍላጎትና ክምችት፣ መጋዘን አያያዝ እና ስርጭት አስተዳደር ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች በየጊዜው እየተሻሻሉ እንዲሄዱና ዘመናዊ አሰራር እንዲሰፍን ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎችን በአገልግሎቱ የእቅድ ክትትል እና ግምገማ ማዕቀፍ መሰረት በማድረግ መለካት አለበት።

CHAPTER FIVE
Miscellaneous Provisions

24. Key Performance Indicators

Activities carried out at the Service's Head Office and Branches with respect to pharmaceutical demand and inventory, warehouse management, and distribution management must be measured using key performance indicators, based on the Service's plan monitoring and evaluation framework, so that they may be continuously improved and modern practice established.

25. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

1/ የሚከተሉት መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡-

ሀ/ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች መጋዘን አያያዝና ክምችት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 352/2013፤

ለ/ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች ሥርጭትና የመኪና ስምሪት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 355/2013፤

ሐ/ የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የግዥ ትንበያ እና የገበያ ጥናት ስራ መመሪያ ቁጥር 384/2013፡፡

2/ ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

25. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The following Directives are hereby repealed by this Directive:

a/ The Pharmaceutical and Medical Equipment Warehouse Management and inventory management directive, registered as Directive No. 352/2021;

b/ The Pharmaceutical and Medical Equipment Distribution and fleet management Directive, registered as Directive No. 355/2021;

c/ The Pharmaceutical Fund and Supply Agency Procurement Forecasting and Market Study Directive, registered as Directive No. 384/2021.

2/ Any directive or practice inconsistent with this Directive shall not apply with respect to matters covered by this Directive.

26. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በአገልግሎቱ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

26. <u>Effective Date of the Directive</u>

This Directive shall enter into force as of the date it is registered with the Ministry of Justice and posted on on the website of the Service.

አዲስ አበባ
መስከረም፣ 2019 ዓ.ም

ዶ/ር አብዱልቃድር ገልገሎ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት

ዋና ዳይሬክተር

Addis Ababa
September, 2026

Dr. Abdulkadir Gelgelo

Ethiopian Pharmaceuticals Supply Service

Director General